## የጥፍጥፍ ወርቅ በባሌስትራ መቀየር ጨዋታ አጥቂ የነበረውና ከጥቁር ገበያ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እንዲወረስ ያደረገው ተስፋዬ መረሳ የሚምልበትን ወያኔን ከዳ

ከዚህ ቀደም የአዲስ አበባው ፖሊስ ኮምሽነር ተስፋዬ መረሳ ከአገሪቱ ብሄራዊ ባንክ የተዘረፍ ወርቅ ባሌስትራ ሆኖ ከመገኘቱ ጋር በተያያዘ የተጠርጣሪነት ቃሉን እንዲሰጥ ተደርጎ እንደነበር መዘገባችን ይታወሳል።

ተስፋዬ መረሳ ከአንድም ሶስት ግዜ ቃሉን ከሰጠ በሁዋላ ምንም የተባለው ነገር ባይኖርም ከእነአዜብ መስፍን የወርቅ ዘረፋ ጋር በተገናኘ ተባባሪና ምስጢር ሽፋኝ ከመሆን አልፎ ከባድ የሆነ ከለላ ይሰጥ ነበር የሚሉ የታመኑ ውስጥ አዋቂዎች አሉ።

ተስፋዬ መረሳ ከጥፍጥፍ ወርቅ በባሌስትራ መቀየር ጨዋታ በተጨማሪ በቅርቡ እርሱ በሚመራው ኮማንድ ፖስት አማካኝነት የጥቁር ገበያ ምንዛሪ ትሰራላችሁ በማለት የዜጎችን አንጡራ ሃብት በመዝረፍ እና በመውረስ ኪሱን ካደለበ በሁዋላ እና ለሃሳቡ አመንጪ የስብሃት ነጋ ሰዎች ድርሻቸውን ከከፈለ በሁዋላ ግምቱ ያልታወቀ የዜጎች ገንዘብና የአገሪቱን ሃብት እንዲሁም በኤግዚቢትነት ተይዘው የነበሩትን ሳይቀር ይዞ መሰወሩና ከአገር መውጣቱ ለአዲስ አበባ ፖሊስ ቅርበት ያላቸው የታመኑ ውስጥ አዋቂዎች አጋልጠዋል። ወያኔዎች የድርሻቸውን እያነሱ ኪሳቸውንና ሆዳቸውን ሲቀበትታቸው ከአገር ለመውጣት መጣደፋቸ በተስፋዬ መረሳ የተጀመረ ባይሆንም የሆነው ግን ወያኔ እየዘቀጠና እየከሰረ መምጣቱን ያሳያል ተብሎዋል።